ዲያቆን ሰሎሞን ዮሐንስ
0911860113
0111/271606
D.N. Solomon Yohannes

# ርእዩ ጽጌያተ ገ[illegible]

## የዱር አበባዎችን ተመልከቱ ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ
በነገሡ በ፴፫ኛው ዘመነ መንግሥት በ፲፱፻፶፫ ዓ· ም·

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት
የኢትዮጵያ ፓትረያርክ በሆኑ በ፪ኛው ዓመት ፤

ይህ መጽሐፍ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን
ጠ| ቤ| ክ| ከታሪክና ድርሰት ክፍል ተዘጋጅቶ ፤
በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አዲስ አበባ መስከረም ፱ ቀን ፲፱፻፶፫ ዓ. ም.

ዲያቆን ሰሎሞን ዮሐንስ
D.N. Solomon Yohannes

www.ethiopianorthodox.org



የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት አልጋ ወራሽ
ልዑል መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ኃይለ ሥላሴ ።

www.ethiopianorthodox.org

★ ዲያቆን ሰሎሞን ★ D.N 0911860123



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት
ወፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ።

www.ethiopianorthodox.org

# ርእዩ ጽጌያተ ገዳም ።

## የዱር አበቦችን ተመልከቱ ማቴ ፳፩. ፩-፲፯ ።

በየዘመኑ ለተነሡ ሰዎች አበቦች በጣም አስደስተ ዋቸዋል ብዙም አስተምረዋቸዋል ።

ከፍ ያለ ውበትንና ሥነን የተጐናጸፈው ጥበበኛ እጁን ያላሳረፈበትን የዱር አበቦች ጌጥ ተመልክተው እጅግ ይደሰቱ እንደነበር ታውቋል ።

በዚህም ምክንያት በሚአብቡበት ወራት ወዳጅ ለወ ዳጁ ፤ ልጅ ለአባቱ ፤ ሎሌ ለጌታው ፤ ደንገጡር ለእመቤትዋ አበቦችን እየቀረጡ ፤ በልዩ ልዩ መልክ እያሠሩ የደስታና የአክብሮት መግለጫ ይሆናቸው ዘንድ ያበረክቱ ነበር ። ከዚህም አልፈው ሕዝብና ካህናት በአንድነት ሁነው ለን ጉሦቻቸውና ለንግሥታቸው በክብር ምልክታቸው በዘውዳ ቸው አምሳል አበቦችን እያሠሩ ወደ ቤተ መንግሥታ ቸው እየሄዱ «ተቀጸል ጽጌ አሄጌ» የሚለውንና ሌላም እሱን የመሰለ መዝሙር እየዘመሩ ደስታቸውን ከፍ ባለ ሁኔታ ሲገልጡ መኖራቸው የታወቀና የተለመደ መሆኑ ግልጥ ነው ።

ይህ ልማድ መቼ እንደተጀመረ ለማወቅ እጅግ አዳ ጋች ነው ፤ ሁኖም የሰው ስሜት ሥነ ጥበብን ማጥናት ከጀ መረበት ጊዜ አንሥቶ ነው ብንል የተሻለ አስተያየት መስሎ ታይቶናል ፤ ይሁን እንጂ ይህ የአበባ መታሰቢያ የተሰጠው ሰው የወዳጁ ፤ የዘመዱ መታሰቢያ በመሆኑ በአበቦች ማስቀመጫ አድርጎ ፤ ውኃ ጨምሮ ለብዙ ጊዜ

www.ethiopianorthodox.org

ንጉሥ ነግሠው ነበር ። እኒህ ንጉሥ ከጀግንነታቸውና ከሀገር ፍቅራቸው ሌላ ሙዚቃ ይወዱ ነበር ፤ ቤተ ክርስቲያንንም ከመጠን በላይ የሚያፈቅሩ ፤ ክርስቲያናዊ ልቡና የነበራቸው አስተዋይ ንጉሥ እንደነበሩ ይነገራል ።

በዘመናቸው «ያሬድ» የተባለው ኢትዮጵያዊ ሊቅ ኑሯል ፤ እርሳቸው ይህንን የተማረ ሊቅ ወደቤተ መንግሥታቸው እያስጠሩ በየጊዜው ልዩ ልዩ ዜማዎችን እያሰሙ ልቡናቸውን በጣዕመ ዜማ ሲያረኩቸው ኑሯል ።

አንድ ጊዜ ግን ይህንን የአበባ በዓል በሚያከብሩበት ዕለት ተገኝቶ «ተቀጸል ጽጌ ገብረ መስቀል ዓፄጌ» ብሎ ዘምሮ ንጉሡን ከልክ ባለፈ ደስታ እንዳስደሰታቸው ይነገራል ።

ይሁን እንጂ ቅዱስ ያሬድ የዚህ ልማድ ጀማሪው አይደለም ። ከዚያም በፊት ሕዝቡ በስድ ንባብ ወይም ባልተቃና ዜማ ሲጠቀምበት የነበረውን የደስታ መግለጫ ቃል ቅዱስ ያሬድ በአማረና በለዘበ ዜማ አዚሞ ቃል ማለት ነው ።

ከዚያ ሲያያዝ በመጣው ልማድ መሠረት ዛሬም በሀገራችን የቤተ ክርስቲያናችን ካህናት ዜማውን በማለዘብ በልዩ ዘዴ የተጌጠውን ቀጭን ኩታና ካባ ለብሰው በንጉሠ ነገሥቱ ፊት ቆመው በመዘመርና ልዩ ልዩ ተሐውሶዎችን በማድረግ የሚያሳዩት ውዝዋዜ ቀላል አይደለም የብዙዎችን የውጭ አገር ተመልካቾች ልቡና ማርኳል ፤ ያላዩትም እንግዶቻችን ለማየት ሲሉ ከሩቅ አገሩ



ቸው ተነሥተው ብዙ ወጭ አድርገው እንዲመጡና እንዲመለከቱ ግድ ሆኖባቸዋል ።

ይህ የተቀደሰ ልማድ እንዲቀጥል የንጉሠ ነገሥታችን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መልክም ፈቃዳቸው ሆኖ በመገኘቱ እነሆ የበዓሉ አከባበር በየዓመቱ በሚበልጥ ሁናቴ እንደቀጠለ ነው ።

የሚከበርበት ዕለት መቼ ነበር ? እንደ ሀገራችን አቈጣጠር በዓተ ክረምት ሰኔ ፳፭ ሲሆን ፀዓተ ክረምት ደግሞ መስከረም ፳፭ ነው ።

ይህ የአበባ በዓልም ለብዙ ጊዜ መስከረም ፳፭ ሲከበር ኑሯል ። ነገር ግን በዓፄ ዳዊት ዘመነ መንግሥት ከመስከረም ፳፭ ወደ መስከረም ፲ ተዛውሯል ። የበዓሉም ስም ተቀጸል ጽጌ ፤ ዓፄ መስቀል ተብሎ ተሠይሟል ። ይህም የሆነበት ምክንያት ዓፄ ዳዊት የጌታ ግማደ መስቀሉ ከኢየሩሳሌም እንዲመጣላቸው ጠይቀው ከብዙ ድካም በኋላ መስከረም ፲ ቀን ደርሶላቸው ክርስቲያናዊ መንፈሳቸው በጣም ተደስቶ ታላቅ በዓል ማድረግ ጀምረዋል ።

በዚህ ጊዜ መኳንንቱና ካህናቱ በአንድ ወር ውስጥ ሁለት በዓል ማድረግ አስቸጋሪ መሆኑን ተገንዝበው የጥንቱ በዓል የሚከበርበት ቀን ተለውጦ ከአዲሱ ከመስቀል በዓል ጋር አጣምረው በአንድነት እንዲከበር ወስነዋል

ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የጥንቱ የአበባ በዓልና የመ

www.ethiopianorthodox.org

ስቀል በዓል በአንድነት ሲከበሩ ኖረዋል ስማቸውም የሁለቱም ሳይቀር አንድ ጊዜ «አጼ መስቀል» ፤ አንድ ጊዜ «ተቀጸል ጽጌ» በመባል ቆይቷል ።

እንዲህ ያለው በዓልን ከበዓል ጋር የመጨመሩ ልማድ እንደ እንግዳ ደራሽ ፤ እንደ ውኃ ፈሳሽ ሳይሆን በሀገራችን የተለመደ ነው ።

ለምሳሌ ያህል የጥምቀትንና የቃናን በዓል አስረጅ ብንወስድ በቂ አስረጅ ለመሆን ይችላል ፤ ይሁን እንጂ ይህ በዓል በጣም አስደሳች በዓል መሆኑ የታወቀ ነው ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ምን እንልበስ ? ፤ ምን እንብላ ?» በማለት በተስፋ መቍረጥ ባሕር ሰጥመው የሚገኙትን አሕዛብ በሚረዱትና በሚያውቁት ምሳሌ ለማስረዳት ፈልጎ «የዱር አበቦችን ተመልከቱ፤ አይፈትሉ ፤ ሸማ አይሠሩ ፤ ነገር ግን ሰሎሞን እንኳ በዚያ ሁሉ ክብሩ እንደ አንድዋ አበባ አድርጎ አጊጦ አያውቅም ፤ እነዚህን የዱር አበቦች እንዲህ ባለ ጌጥና ጥበብ የሚያስጌጥ አባታችሁ እግዚአብሔር እያለ እንዴት ምን እንለብሳለን ? ምን እንበላለን ? እያላችሁ ትጨነቃላችሁ ? እናንት ሃይማኖተ ጎደሎች» ብሎ ወቅሶአቸዋል ፤ በተለየም አበቦችን በመመልከት ልናስብ ፤ ልንረዳ ፤ ልንጠይቅ ፡ ልንመረምር ተገቢ መሆኑን ያስረዳል ፤ የእግዚአብሔርም ጥበብ ከፍ ያለ መሆኑን ያስተምረናል ።

በዚህ ዓለም ታላላቅ ሰአሊዎች ተነሥተዋል ፤ ቢሆንም ጥበባቸው የሚደነቀውና የሚመሰገነው የእግዚአብ



ሔርን ጥበብ አስመስለው በመሣላቸው ብቻ ነው እንጂ ወደ ሥነፍጥረት ውበት ትክክለኛ ደረጃ ገና አልደረሱም።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «አበቦችን ተመልከቱ» ማለቱ የተስፋ ምልክቶች እንዲሆኑን ነው ።

እነሱ ሳይፈትሉ፤ ሸማኔም ሳይኖራቸው እንዲህ ያለ አስደናቂ ጌጥ ያለው ልብስ የሚያገኙ ከሆነ ፡ እኛም ምን እንለብሳለን ? በማለት እንዳንጨነቅ የፈጠረን አምላክ ለአዕዋፍ ምግባቸውን ፤ ለተራሮችና ለኮረብቶች ልብሳቸውን ሳይጠይቁት፤ ሳይወጡ፤ ሳይወርዱ እንደሚሰጣቸው ተመልክተን ፡ እኛም ተስፋችንንና እምነታችንን በእግዚአብሔር እንድናደርግ የሚያስረዳ ጥልቅ ምሥጢርን የተመላ ታላቅ በዓል ስለሆነ ፡ በሰቂለ ኅሊና ሥነ ፍጥረትን በመመልከት ዓይነ ልቡናችንን ወደ እግዚአብሔር እንድናቀና ያስታውሰናል ። ልዑል እግዚአብሔር በዚህ ዕለት የተጸለየውን ጸሎት፡ የተሠዋውን መሥዋዕት ተቀብሎ ለንጉሠ ነገሥታችን ረጅም ዕድሜና ጤና ፤ ለሀገራችንና ለእኛም ሰላምና ብልጽግና እንዲሰጠን እንለምነው ።

ምዕራፍ ፪ ።

በተለይ መስከረም ፲ ቀን «ተቀጸል ጽጌ አጼጌ» ብለን የምናከብረው ከጥንት ሲያያዝ የመጣውን የሰሎሞንን ታሪክና መጽሐፍ በመመልከት ነው ሰሎሞን የአባቱን መንግሥት እጅ ካደረገና ሕዝቡም እንደተቀበሉት አይቶ የክረምት ወራት አልፎ የበጋ ወራት የሚጀመርበትን የመጀመሪያውን ዘመን ያከብረውና ያስከብረው ነበር ።

ንጉሡ ሰሎሞን አምስት መቅረዝ በቀኝ ፡

www.ethiopianorthodox.org

አምስት መቅረዝ በግራ የሚገኝበት ተቀዋም አሥርቶ እሱ ከመከከሏ ይቀመጣል ፤ ልብሰ መንግሥቱንም ለብሶ ለሕዝቡና ለመኳንንቱ ይታይ ስለነበር ሕዝቡ ተሰብስበው ካህናቱም ተስማምተው «ተቀጸል ጽጌ»ብለው አመስግነውታል አምስት መቅረዞች በስተቀኝ ፤ አምስት መቅረዞች በስተ ግራ ከፍ ባለ ሥፍራ ፊት ለፊት ከአበቦችና ከግብሪያዎችም፤ ከመከስተሪያዎችም ጋራ ሁሉን ከጥሩ ወርቅ አደረገ ይላል አንደኛ ነገሥት ፯ ፵ ፱ ነገሥታት ይህን በዓል ከፍ ባለ ክብር ማክበራቸው በዚህ ዘመን ጽጌያት በአማረ አበባና በመልካም ሽታ አጊጠውና አሸብርቀው ስለሚታዩ ነው ፤ በዚሁ ዕለት ነገሥታቱም ልብሰ መንግሥታቸውን ለብሰው እንደ ጽጌያት አብበውና አሸብርቀው ከፍ ባለ አክብሮት ለሕዝቡና ለካህናቱ ይገለጣሉ ፤ ሕዝቡም «ዘመኑን ዘመነ ሰላም፤ዘመነ ተድላ ያድርግልን፤ለንጉሣችንም ዕድሜና ጤና ይስጥልን»ይላሉ ። ወዲያው ካህናቱ ልብሰ ተክህኖ ለብሰው፤ መዘምራኑም ለበዓሉ ተስማሚ የሆነውን ቀለም ከመጽሐፍ ቅዱስ እያወጣጡ ጣዕም ባለው ዜማ ሲያሸበሽቡ ይውላሉ ። ይህን አርዓያና ምሳሌ በመከተል የኢትዮጵያ ነገሥታት መስከረም ፲ ቀን ወርቅና ብር የተሳለባቸውን ልብስ ለብሰው ፤ በዙሪያው አበባ የፈነዳበትን መንበር ተጐናጽፈው ፤ ከፍ ባለ ቦታ ላይ ሆነው ለሕዝቡ ይታያሉ ።

በዚህ ዓመት ከአባቶቻችን ሲያያዝ የመጣልንን ይህንን በዓል ለማክበር ስላአበቃን ፤ እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው ። አሜን



ምዕራፍ ፫ ።

ከመናገሻ ቅዱስ ጊዮርጊስ ደብር (ገነተ ጽጌ)
ካህናት የተዘጋጀ ።

ስለ ፲፱፻፶፮ ዓ. ም. የአጼ መስቀል በዓል አከባበር፤
ጽዋትወ ዜማ ፤ ምስባክና ወንጌል ።

፩ኛ ምስባክ ።

ተስፋሆሙ ለኵሎሙ አጽናፈ ምድር ፤
ወለእለሂ ውስተ ባሕር ርሑቅ ።
አጽናዕከሙ ለአድባር በኃይልከ ።

የምስባኩ ትርጓሜ ።

ለምድር ዳርቻና በሩቅ ባሕር ላሉ ሁሉ ተስፋቸው፤ አለኝታቸው አንተ ነህ ፤ በኃይልህ፤ በጉልበትህ ተራሮችንም ያጸናህ አንተ ነህ» ብሎ ነቢዩ ዳዊት እንደ ተናገረው፤ ግርማዊነትዎም በኢትዮጵያ ለአፍሪካውያን መሪ ሆነው ኅብረትን፤ አንድነትን ማጽናትዎን ይገልጻል ።

፪ኛ. ወንጌል ዘማቴዎስ ምዕራፍ ፭ ቍጥር ፲፬—፲፯ ፤

አንትሙ ውእቱ ብርሃኑ ለዓለም ፤ ኢትክል ተከብቶ ፤ (ተኀብአ) ሀገር እንተ መልዕልተ ደብር ትነብር ፤ ወኢየኃትዉ ማኅቶተ ከመ ያንብርዋ ታሕተ ከፊር ፤ አላ ያንብርዋ ዲበ ተቅዋም፤ ወታበርህ ለኵሎሙ እለውስተ ቤት ከማሁ ይብራህ ብርሃንክሙ በቅድመ ሰብእ ከመ ይርአዩ ምግባሪክሙ ሠናየ ወይሰብሕዎ ለአቡክሙ ዘበሰማያት ።

የወንጌሉ ትርጓሜ ።

እላንት የዓለም ብርሃን ናችሁ ፤ በተራራ ላይ የተሠ

www.ethiopianorthodox.org

ራች አገር መሠወር አይቻላትም ፤ መብራትም በመቅረዙ ላይ እንጂ በእንቅብ ውስጥ ሊያኖሩት አያበሩም ፤ በቤት ላሉት እንደሚያበራ እንዲሁ ብርሃናችሁ በሰው ፊት ይብራ ፤ መልካሙን ሥራችሁን አይተው የሰማይ አባታችሁን ያመሰግኑት ዘንድ ።

ይህ የወንጌል ቃል የሚያሳስበው ግርማዊነትዎ ለአፍሪካውያን ብርሃናዊ መሪ ሆነው ባደረጉት ታሪካዊ ሥራ ኢትዮጵያ ከአፍሪካውያን ጋር በፍቅር አንድ ሆና ፥ ስለ ዓለም ሰላም ተባብራ መሥራቷን ያመለክታል ።

## ፫ኛ. እስመ ለዓለም ።

ለሰሚዕ ዕፁብ ግብር ፤ ለሰሚዕ ዕፁብ ግብር ጥበቡ ለእግዚአብሔር(ለ)አጽናፈ ዓለም እለ ተዘርወ ለስብከተ ወንጌል አስተጋብኦሙ በምዕር፤(ለ)በእለ ተንሥኡ ተጽኢኖሙ ደመና ብሩህ (ለ) ወተፈሥሐ ሐዋርያት ሶበ ተጋብኡ ኅቡረ ገብሩ በከመ አዘዘሙ ፤ ወከመ ቀዳሚ ተመይጡ ኵሎሙ ።

## ግ ሥ ።

ለሰሚዕ ዕፁብ ግብር ጥበቡ ለግዚአብሔር አጽናፈ ዓለም እለ ተዘርወ አስተጋብኦሙ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ፤ ገብሩ በከመ ይቤሎሙ ፤ ወከመ ቀዳሚ ተመይጡ ኵሎሙ በጸሎተ ባስልዮስ ር. ሊ. ጳ.

## ፬ኛ አቡን በ፩ ።

ኃበሩ ቃሎሙ ፥ ወሥርዓቶሙ ተጋቢኦሙ ነገሥታተ ምድር፤ኃይል ወሥርዓት ይሠምር በሙ ፤ እምነ ፀሐይ ይበ



ርህ ገጾሙ ወድሙር ኵሉ ንዋዮሙ ገብሩ በከመ አዘዘሙ ።

## ፭ኛ. አራራይ እስመ ለዓለም ።

ድሙር ማኅበሮሙ ፤ ክርስቶስኒ ሠርዐ ምስሌሆሙ፤ ጸውኦሙ ፤ ወባረኮሙ ፤ ወይቤሎሙ አማልክት አንትሙ፤ ወደቂቀ ልዑል ኵልክሙ ፤ ወሰኑ ወሠርዑ ሃይማኖተ (ሥርዓተ) እንተ ኢትጠፍዕ ።

## ፮ኛ. ቅ ን ዋ ት ።

ሠላሳ ወክልዔቱ ድሙር ማኅበሮሙ ክርስቶስሃ ተወኪሎሙ ፤ ዕፀ መስቀሉ ተመርጕዘሙ ፤ ሞዑ ፤ አግረሩ ፀሮሙ ፤ ጌራ መድኃኒት ዲበ ርእሶሙ ።

## ፯ኛ ሥ ለ ስ ት ።

በዕፀ መስቀሉ አስተጋብኦሙ ለብዙኃን ነገሥት እንዘ ሀሎ ኃይለ ሥላሴ ማዕከሌሆሙ ከመ ዘአሐዱ እምኔሆሙ ፤ ወሰኑ ፤ ወሠርዑ ሃይማኖተ ሥርዓት እንተ ትፈሪ ሕይወተ ።

## ፰ኛ. ሰ ላ ም ።

አስተጋብኦሙ እምበሐውርት፤እምጽባሕ፤ወእም ዓረብ፤ ወመስዕ ፤ ወባሕር ፤ እስመ ብርሃነ ኮነ ለኵሉ ዓለም ፤ ወነገሮሙ ነገረ ሰላም ።

## የእስመ ለዓለምና የግሥ አጭር መግለጫ ።

ሊቁ ቅዱስ ያሬድ እንደተናገረው ግርማዊነትዎም ተበትነው የነበሩትን (የሚኖሩትን) አፍሪካውያንን ነፃነታቸውን ተጐናጽፈው ፤ ሀብትና ሥልጣኔን አስፋፍተው እንዲኖሩ ማድረግዎን ያሳያል ።

www.ethiopianorthodox.org

## ፩ኛ| መወድስ ።

መፍትው ትትመከህ በኃይለ ሥላሴ ፡ ኢትዮጵያ ዘክህለት ፡ ለአፍሪካውያን ጉባኤሆሙ ። እስመ በውስቴታ ተሰምዐ ፡ ጽድቀ ግዕዛኖሙ ። ወንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ ፡ በኢዮቤልዩ አጽደቀ ስምአሙ ።

ለኢየሩሳሌም ኢዮቤልዩ፡እስመ ትርጓሜሃ ሰላም፡ለአፍሪካውያን ኮሎሙ ።

## ለዓለም ፡

ወመልአከ ሰላም ኃይለሥላሴ፡ ኀሩየ ኀሩያን ቀዲሙ።
ለአፍሪካውያን ሰብአ ጉባኤ፡በደመና ግዕዛን ይመርሆሙ፡
እስመ በግርማሁ ተርጐመ ፡ ከመ ዳንኤል ቃሎሙ ።
ወስብከተ ባስልዮስ ድኅረ ሰምዑ ፡በፍኖተ ሰላም ፈነዎሙ ።

ሊቀ ጠበብት ተ| ሚካኤል ።

## ፪ኛ| መወድስ ፡

ትቤሎሙ ቃለ እምትእዛዛቲከ፡ለእለ ጉቡአነ ክኑ፡አነ ቀዳማዊ ። ኃይለ ሥላሴ ሕያው ፡ እንዘ ደኃራዊ ።

ወእንዘ ከብካብ ሕብረትነ ፡ መርዓት ፍቅረ እንቲአነ ወአነ መርዓዊ ። መዓልተ ወሌሊተ ፡ በስብከተ ቅዱስ ባስልዮስ ፡ ዮሐንስ ወንጌላዊ ።

## ለዓለም ፡

ይቤሉከሂ ኀሩያኒከ ፡ ኃይለ ሥላሴ ግርማዊ ።
ፈኑ ብርሃነከ ፡ ምስለ ጥበብከ መንፈሳዊ ።
አመኒ መጻእከ ምስለ ወልድከ ዜናዊ ።
ላዕለ ታቦር ዘመንከ፡ ዓርገ ቴስብያዊ ። አባ ተ| ሃይማኖት ።



## ምዕራፍ ፬ ።

### ስለ ተቀጸል ጽጌ በዓል ከጥላሁን ገብረ መድኅን የተደረሱ ቅኔዎች ።

## ፩ኛ መወድስ ።

እግዚአብሔር ርኢነ ገጸ ተበርዮ ፡ ወሥነ ተውላጥ ነጸርነ ፡ በመድሎትከ መጽሔት ።
ዘናንሶሱ ንሕነ ፡ በፍኖተ ዓለም ዕቅፍት ።
ዘሰ ናጠይቅ ፡ ለሕይወት ጊዜ ፡ ወጊዜ ለሞት ።

ወኀበ ዘተውላጥ ዓለምነ ፡ ለወርኀ ጼዋዌ ብዙኀ ፡ እስመ ይተልዎ ሚጠት ።

## ለዓለም ።

ናእምርሂ ምጣኔሃ ፡ ለተበርዮ ዕምርት ።
ዓመተ አፍሪካ ዓመተ ፍዳ ፡ እምቅድመ አውራኀ ወአዝማናት ።
ይእዜሰ ኮነ ፡ ዓመተ ምሕረት ።
አክሊለ ግዕዛን ለፍጻሜ ፡ አምጣነ አፍሪካ ተቀጸለት ።

## ፪ኛ መወድስ ።

ትፍሥሕት ይሰፍን እምድኅረ ሀለፈ ፡ መዋዕል ዘላህ ፡ ወአመ ተፈጸመ በኃዘን ።
ዓመተ ግፉዓን ሰማዕት አፍሪካውያን ።
አንሥአ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ኄራን ።
ቆስጠንጢኖስሃ ኃይለ ሥላሴ ፡ ወበትእዛዙ ተገብረ ፡ ጉባኤ ነገሥት ኅሩያን ።

www.ethiopianorthodox.org

## ለ ዓ ለ ም ።

እንከሰ ኢየሐውሩ ፣ ዐውደ ከነዓን ።

ዘማዕዶተ ባሕር ዕፃሆሙ፤ ሕዝበ ያሬት ክልአን።
አኮኑ አድምኡ ፣ ተስፋ ግዕዛን ።

ወለብሱ ድርዐ ጽድቅ፤ ነገሥተ አፍሪካ መዋዕያን።

## ፫ኛ መ ወ ድ ስ ።

ኃይለ ሥላሴ ህልው በኃይለ ሥላሴ ፣ ሰላም ወሕግ፡
መሰክወ ቤትከ ያሰምከ ።

ቅድመኒ ተረክቡ ፤ በልቡናከ ታዕከ ።

ፍቅረ ሰብእ ዊዋ ፣ ወሰላም ምህርከ ።

እንከሰ እስከ ፍጻሜ ፣ ለአፍሪካዊት ምድር ፣ ጸላኢ
ኢየሐውከ ።

## ለ ዓ ለ ም ።

ማዕዶትሂ ትርጓሜሁ ፤ ለመንግሥትከ ፋሲካ ።

ቦቱ እስመ ዓደውነ፤ እሞተ ግብርናት ሕዝበ አፍሪካ።

ቃላቲከሰ ዘነሥአ ማኅቶተ ትንቢት ዋከ ።

ግዕዛነ ይዜንዋ ፣ ወሰላመ ይሰብከ ።

ዲያቆን ሰሎሞን ዮሐንስ
Solomon Yohannes

www.ethiopianorthodox.org